የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ

# ቁጥር 14/ 2013 ዓ.ም.

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1. አውጪው ባለስልጣን**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ (3) እና አንቀፅ 57 ንዑስ አንቀፅ (4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

**አንቀፅ 2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ***«የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 14/2013»*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀፅ 3. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው።
2. "**ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3. **"ታዛቢ"** ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጪ የምርጫ ታዛቢ ማለት ነው።
4. **"የእጩ ወኪል"** ማለት ተቀማጭ ወይም ተንቀሳቃሽ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወኪል ማለት ነው።

5. በአዋጁ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደ አግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**አንቀፅ 4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ ጠቅላላ ምርጫ እና እንደአግባብነቱ በአካባቢ ምርጫ፣ በድጋሚ ምርጫ፣ በማሟያ ምርጫ እንዲሁም በሕዝበ ውሣኔ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 5. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውን ፆታም ያካትታል።

**አንቀጽ 6. <u>ዓላማ</u>**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የድምፅ አሰጣጥን፣ ቆጠራን፥ የምርጫ ውጤት ማዳመርና አገላለፅ ሂደት አፈፃፀምን ግልፅ፣ ቀልጣፋ እና ወጥነት ያለው ማድረግ፤ መራጮች፥ ተወዳዳሪዎች፥ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የእጩ ወኪሎች፣የፓርቲ ወኪሎች፥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፥ የአገር ውስጥና የውጪ ታዛቢዎች በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ እንዲሁም የምርጫው ሂደት፥ ሁሉን ዓቀፍ፥ ነፃ፣ ፍትሀዊ ተአማኒ፥ ሰላማዊ እና ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ነው ።

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>ስለድምፅ አሰጣጥ ጠቅላላ</u>

**አንቀፅ 7. <u>የምርጫ ጣቢያ አካላት አደረጃጀት</u>**

1. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ እንደአግባብነቱ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 6(1) ለቦርድ አባላት ምልመላ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ቢያንስ አንድ ሴት ያካተተ፥ አምስት የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚገኙበት የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፤
2. ኮሚቴው ከአንድ በላይ ሴት የምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲኖሩት ጥረት ይደረጋል።
3. የምርጫ ጣቢያውን ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሰብሳቢነት በመምራት የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ማን እንደምትሆን ከምርጫ ቀኑ አስቀድሞ የምርጫ ክልሉ ፅ/ቤቱ ለጣቢያው ማሳወቅ ይኖርበታል።

4. አንድ የምርጫ አስፈፃሚ በድምፅ መስጫ እለት በሥራዋ ላይ መገኘት ካልቻለች የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ወዲያውኑ በተጠባባቂነት ከተያዙት የምርጫ አስፈፃሚዎች መካከል ለተጓደለችው የምርጫ አስፈፃሚ የተሰጡትን የስራ ተግባራት ለማከናወን በምትችል የምርጫ አስፈፃሚ እንድትተካ ታደርጋለች።
5. በምርጫ ጣቢያው በተጠባባቂነት የተያዘች የምርጫ አስፈፃሚ ከሌለች በፍጥነት ለምርጫ ክልሉ በማሳወቅ እንድትተካ ታደርጋለች።

## አንቀጽ 8. <u>በድምፅ መስጫ እለት የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች ስልጣንና ኃላፊነት</u>

በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች በድምፅ መስጫ እለት የሚከተሉት ዋና ዋና ኃላፊነትና ስልጣኖች አሏቸው።

### 1. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ

ሀ) የምርጫ ጣቢያውን ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሰብሳቢነት መምራት፤

ለ)የምርጫ አስፈፃሚዎች የተመደቡበትን የስራ ሃላፊነት በአግባቡ መወጣታቸውን መቆጣጠር እና መከታተል፤በአስፈፃሚዎች የሚፈፀሙ ስህተቶች ሲኖር የእርምት እርምጃ መውሰድ፤

ሐ)ከፍተኛ የሆነ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት በአስፈፃሚ ተፈፅሞ ሲገኝ ለምርጫ ክልል ሀላፊ በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፤

መ) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ጨምሮ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ሥልጣንና ኃላፊነቶች እንዲያከናውኑ የተመደቡ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች ሲጓደሉ በምርጫ ጣቢያው ወይም በምርጫ ክልሉ በተጠባባቂነት ዝርዝራቸው ከተያዙ ምርጫ አስፈጻሚዎች ጠይቆ መተካት፤

ሠ) ከድምፅ አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ገለፃዎችን መራጮች ድምፅ ከመስጠታቸው በፊት በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ገለልተኛ በሆነ መልኩ መስጠት፤ይህንን ተግባር ስትተገብርም ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን ፖስተር በአግባቡ በመጠቀም ግልፅ መረጃ ለመራጮች መስጠት፤

ረ) የድምፅ መስጫ ሰነድና ቁሳቁስ ከምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ወደ ምርጫ ጣቢያው በአግባቡ መድረሳቸውን ማረጋገጥ፤ የምርጫ ጣቢያው በድምፅ መስጫ ቀን ጥቅም ላይ የሚውሉ በቂ የድምፅ መስጫ ቁሳቁስና ሰነዶች እንዳሉት ማረጋገጥ፤

ሰ) ከምርጫ ክልል ፅ/ቤት የተረከባቸው ሁሉም ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከድምፅ መስጫ ቀን በፊት ባለው ጊዜ ሁሉ ደህንነቱ በተረጋገጠ ስፍራ በአግባቡ ተጠብቀው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ፤

ሸ) በምርጫ ጣቢያው የድምፅ መስጠት ሂደቱን በሚገባ ለማከናወን የሚያስችል ምቹ የሆነ ስፍራ እንዳለው እንዲሁም በአግባቡ መሰናዳቱን ማረጋገጥ፤

ቀ) በምርጫ ህጉ መሰረት በድምፅ መስጫ እለት በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መገኘት ያለባቸው ሰዎች ብቻ መገኘታቸውን ማረጋገጥ፤

በ) በድምፅ መስጫ ዕለት ጥቅም ላይ የሚውሉ የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶች በምርጫ ማስፈጸሚያ ቁሳቁሶችና እና ሰነዶች ድልድል፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብና አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 8/2013 መሰረት በአግባቡ መያዛቸውን መከታተል ስለአፈፃፀሙም ለምርጫ ክልሉ ሪፖርት ማድረግ፤

ተ) የምርጫ ጣቢያው ደህንነትና ሥርዓት መጠበቁን ማረጋገጥና ይህም እንዲከበር ማድረግ፤ ሰላምና ደህንነት እንዲያስከብሩ ለምርጫ ጣቢያው የተመደቡ የፖሊስ አባላት የእገዛ ጥያቄ በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ካልቀረበላቸው በስተቀር ወደ ምርጫ ጣቢያው አለመግባታቸውን ማረጋገጥ፤

ነ)ወደ ሚስጥር ድምፅ መስጫ ቦታ በአንድ ጊዜ ድምፅ የሚሰጥ መራጭ ብቻ መግባቱን መግባቱን፥ ሌላ ማንኛውም ሌላ ሰው ሚስጥራዊነትን ተግባር እንዳይፈፅምመቆጣጠር፤

ቸ) ድምፅ መስጫውው እለት መጨረሻ ከድምፅ አሰጣጥና ቆጠራ ጋር የተያያዙ ሁሉም መረጃዎች በትክክል መመዝገባቸውን በፍጥነት በማረጋገጥ ሰነዶቹ እና የምርጫ ቁሳቁሶች ለምርጫ ክልል ጽ/ቤቱ ማስረከብ፤ በቦርዱ ወይም በምርጫ ቦርዱ ስልጣን የተሰጣት ሰው የምትሰጣትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

## 2. የመዝገብ ሹም

የመዝገብ ሹም ሆና የተመደበች የምርጫ አስፈፃሚ፡-

ሀ) መራጩ የመራጭነት መታወቂያ ካርድ ይዞ በሚቀርብ ጊዜ ካርዱን ተቀብላ በመራጮች መዝገብ ላይ መረጃውን በመፈለግ መራጯ በአግባቡ የተመዘገበች መሆኑን ታረጋግጣለች፤

ለ) መራጯ ያቀረበችውን የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ፣ በመራጮች መዝገብ ላይ ከሰፈሩት መረጃዎች ጋር በማመሳከር እና በማረጋገጥ እንዲሁም በድምፅ መስጫ እለት መራጯን የማይለቅ ቀለም እንድትቀባ አድርጋ መራጯን በመራጮች መዝገብ ላይ መፈረም በሚገባት የመዝገቡ አምድ ላይ እንድትፈርም ታደርጋለች፤

ሐ) የመራጮችን መዝገብ የድምፅ መስጫው እንዲከናወን በተወሰነበት የጊዜ ገደብ ሁሉ በሚገባ ትጠብቃለች፤

መ) በምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ ወይም በምርጫ ቦርድ ስልጣን የተሰጣት ሰው የምትሰጣትን ተጨማሪ ተግባራት ።

## 3.የሰልፍ አስከባሪ

ሀ) በምርጫ ጣቢያው መግቢያ በር ላይ በመቆም መራጮች ለመምረጥ ሲመጡ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዳቸውን በመመልከትና በምርጫ ጣቢያው የተመዘገቡ መሆናቸውን እንዲሁም የድምጽ ሰጪነት የቀለም ምልክት የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የመራጭ ረዳት ከሆኑ ሰዎች በስተቀር በአንድ ወቅት አንድ ሰው ብቻ ወደ መዝገብ ሹሟ መሄዷን ታረጋግጣለች፤

ለ) ለመምረጥ የሚመጡ መራጮችን እየፈተሸች ወደ ምርጫ ጣቢያው ታስገባለች፤ ወደ ምርጫ ጣቢያ ይዞ መግባት የተከለከሉ የጦር መሳሪያና ስለት ያላቸው ነገሮችን መራጮች ይዘው እንዳይገቡ

ትከለክላለች። ይሁንና በፆታ ልዩነት ምክንያት ለመፈተሽ ፍቃደኛ ያልሆነ መራጭ በሚኖርበት ጊዜ ከሌሎች አስፈፃሚዎች እገዛ ማግኘት ይኖርባታል።
ሐ) ለመምረጥ የሚጠባበቁ መራጮች በምርጫ ጣቢያው መግቢያ ላይ በአግባቡ መሰለፋቸውን እንዲሁም ድምፅ ከሰጡ በኋላ ወዲያውኑ ከጣቢያው መውጣታቸውን ታረጋግጣለች፤ ከኮቪድ 19 መኮንን ጋር በመተባበር ተገቢው ጥንቃቄ መደረጉን ትከታተላለችታስፈፅማለች።
መ) የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን የሚያውክ ሁኔታ ሲፈጠር ለምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ ወዲያውኑ ሪፖርት ታደርጋለች፤
ሠ ) የመራጮች ምዝገባ ካርድ የጠፋባቸው መራጮች ጉዳያቸው እስኪጣራ ተለይተው ወደሚቆዩበት ቦታ እንዲቆዩ ማድረግ ይህንኑ ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ማሳወቅ።
ረ) በምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ ወይም በምርጫ ቦርዱ ስልጣን የተሰጣት ሰው የምትሰጣትን ተጨማሪ ተግባራት ታከናውናለች።

## 4. የድምፅ መስጫ ወረቀት አዳይ/ሰጪ

ሀ) የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ጥራዝ እንዲሁም የቦርዱን ማህተም ከምርጫ ጣቢያ ሀላፊው በመረከብ በጥንቃቄ ትይዛለች ።
ለ) የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ከድምፅ መስጫ ወረቀቶች ጥራዝ ላይ በጥንቃቄ እየነጠለች በጀርባው ላይ የቦርዱን ማህተም አድርጋ ለመራጮች ትሰጣለች፤
ሐ) መራጮች በድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ ምልክት ካደረጉ በኋላ የድምፅ መስጫ ወረቀቱን እንዴት በቁመቱ ወደውስጥ ማጠፍ እንደሚገባቸው ተገቢውን ማብራሪያ ትሰጣለች፤
መ) ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች አስፈላጊው ጥንቃቄ እና ጥበቃ መደረጉን ታረጋግጣለች።

## 5. ድምፅ መስጫ ሳጥን ተቆጣጣሪ

ሀ) በዋነኛነት የድምፅ መስጫ ሳጥኖችን ትቆጣጠራለች፤
ለ) መራጮች በድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ በምስጢር ድምፅ መስጫ ክፍል ምልክት ካደረጉ በኋላ ቀለሙ የተለየውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በትክክለኛው ሳጥን ውስጥ መክተታቸውን ትከታተላለች፤
ሐ) በድምፅ አሰጣጥ ሂደት የድምፅ መስጫ ሳጥኑን ከማናቸውም አደጋ እና የማበላሸት ተግባር ትጠብቃለች፤
መ) ድምፅ ሰጪዎች ከምርጫ ጣቢያው ድምፅ መስጫ ወረቀት አዳይ ከተሰጡ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ውጪ ወደ ድምፅ መስጫ ሳጥኑ አለማስገባታቸውን እንዲሁም የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ከምርጫ ጣቢያው ይዘው አለመውጣታቸውን ትቆጣጠራለች፤

ሠ) መራጮች ከምርጫ ጣቢያው የተሰጣቸውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ወደ ትክክለኛው ድምፅ መስጫ ሳጥን ካስገቡ በኋላ ምርጫ ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ ወደ ምርጫ ጣቢያው መውጫ ትመራለች፤

ረ) ድምፅ መስጫ ሳጥኑ በመራጮች የድምፅ መስጫ ወረቀት ማስገባት የሚያስችል መሆኑን በየጊዜው ቁጥጥር ታደርጋለች፤ የድምፅ መስጫ ሳጥኑ ተጨማሪ የድምፅ መስጫ ወረቀት ለመክተት ለመራጮች የሚያስቸግር ሆኖ ተጨማሪ/ተተኪ የድምፅ መስጫ ሳጥን የሚያስፈልግ ከሆነ ጉዳዩን ለምርጫ ጣቢያ ሀላፊው ታሳውቃለች።

## አንቀፅ 9. <u>የድምጽ መስጫ ቦታ</u>

በተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያ ከተመዘገቡ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ አባላት በስተቀር መራጮች ድምጽ የሚሰጡት በተመዘገቡበት የምርጫ ጣቢያ በዚያው ስፍራ ነው፡፡

## አንቀፅ 10. <u>የድምፅ መስጫ ቀን እና ሰዓት</u>

1. የጠቅላላ ምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ቦርዱ በሚወስነው ቀንና ሰዓት በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች በአንድ ላይ ይጀመራል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ሁኔታው የሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጡን በተለየ ቀን እንዲጀምሩ ቦርዱ ሊወስን ይችላል።
3. በክልል ሕገ መንግስታትና ሌሎች ሕጎች ላይ ተመስርተው የሚካሄዱ የአካባቢ ምርጫዎች ድምፅ አሰጣጥን በተለየ ጊዜ እንዲካሄዱ ቦርዱ ሊወስን ይችላል፡፡
4. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 37 ንዑስ ቁጥር 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የተለየ ውሳኔ ካልወሰነ በስተቀር የማንኛውም ምርጫ የድምፅ መስጫ ሰዓት ከማለዳው 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12:00 ሰዓት ድረስ ነው፡፡
5. ቦርዱ የተለየ የድምፅ መስጫ ቀን እና ሰዓት የወሰነ እንደሆነ የተወሰነውን የድምፅ መስጫ ቀንና ሰዓት ከምርጫው ዕለት ቢያንስ ሰባት ቀን አስቀድሞ መራጩ ህዝብና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በይፋ እንዲያውቁት ያደርጋል።

## አንቀጽ 11. <u>የምርጫ ጣቢያ ዝግጅት</u>

1. የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ ከ 3 ቀናት በፊት መራጩ ህዝብ ድምፅ የሚሰጥበት የምርጫ ጣቢያ ድምፅ አሰጣጡን በሚገባ ለማከናወን በሚያስችል መልኩ ለምርጫ ጣቢያ በተመደቡት የምርጫ አስፈፃሚዎች መዘጋጀት አለበት።

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ጣቢያው ግቢ የሌለው ሲሆን ደ ሞ በጣቢኣው በር እና ግድግዳ ላይ እንደአግባብነቱ የአገሪቱን እና የክልሉን ሰንደቅ አላማ ይሰቅላሉ፤ እንዲሁም ቦርዱ የሚያሰራጫቸውን የተለያዩ ፖስተሮችን በተገቢው ቦታዎች ይለጥፋሉ፡፡
3. የድምፅ አሰጣጡን ሂደት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል ቦርዱ በሚያሰራጨው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስዕላዊ መግለጫ መሰረት ፣

   ሀ) ቦርዱ ለምርጫ ቀን በሚል ያሰራጨውን አግባብነት ያላቸው ቁሳቁሶች በመጠቀም፥ አንድ የሚስጥር ድምፅ መስጫ ስፍራ መዘጋጀት አለበት፡፡

   ለ) የድምፅ መስጫ ሳጥን በጣቢያው እንዲገኙ ለተፈቀደላቸው ወኪሎች እና ታዛቢዎች ሁሉ ፊት ለፊት በቅርብ እይታ እንዲታይ ሆኖ በግልጽ ሥፍራ መቀመጥ አለበት፡፡

   ሐ) በድምፅ መስጫ ጣቢያው መግቢያ አካባቢ ለመራጩ ስለድምፅ አሰጣጡ ገለፃ የሚሰጥበት ስፍራ መዘጋጀት አለበት፡፡

   መ) የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትና ታዛቢዎች የሚቀመጡበትና የድምፅ አሰጣጡን ሂደት በግልፅ ለመመልከት የሚችሉበት፣ የመዝገብ ሹሞች የመራጯን ማንነት ለማረጋገጥ የሚቀመጡበት፣ የድምፅ መስጫ ወረቀት ለመራጩ የሚሰጥበትና የምርጫ ማረጋገጫ ቀለም የሚቀባበት ቦታና መገልገያ ቁሳቁስ ተለይተው በሚገባ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

4. ምርጫ አስፈፃሚዎች መግቢያና መውጫው የተለያየ የድምፅ መስጫ ስፍራ ወይም ቤት ወይም ድንኳን ወይም ዳስ ያዘጋጃሉ፡፡
5. በዚህም መሰረት ምርጫ አስፈጻሚዎችና ከላይ የተገለጹ ሌሎች ሰዎች የቦታው አቀማመጥ በተቻለ መጠን መራጯ ድምፅ ከሰጠች በኋላ ድጋሚ ወደ የድምፅ መስጫ ሳጥን ወደሚገኝበት ስፍራ ለመመለስ የማያስችል መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
6. ከላይ የተገለጹትን አስፈላጊ ቦታና ቁሳቁስ፥ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች የምርጫ ጣቢያው የተቋቋመበትን ስፍራ ለቦርዱ ከሰጠው ኃላፊዎች ጋር በመተባበር ማሟላት ካልቻሉ በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አማካኝነት ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ወዲያውኑ በማሳወቅ ችግሩ እንዲቀረፍ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባት፡፡
7. የምርጫ አስፈጻሚዎች ለድምፅ መስጠት ሂደቱ የተለያዩ ተግባራት ተለይተው የተዘጋጁትን ቦታዎች ለመለየት የሚያስችሉ ከቦርዱ የሚላኩ መለያ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣ መለጠፍ ወይም መስቀል ይኖርባቸዋል፡፡
8. የምርጫ አስፈጻሚዎች ለየምርጫው ዓይነት የእጩዎችን ስም፣ መወዳደሪያ ምልክቶችን እና ፓርቲያቸውን ወይም በግል ተወዳዳሪ መሆናቸውን ማስተዋወቂያ ፖስተር እንዲሁም የድምፅ አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ የያዙ ፖስተሮች ለመራጩ ገለፃ በሚደረግበት ቦታ፣ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ማንጠልጠል አለባቸው፡፡

### አንቀፅ 12. <u>የድምፅ መስጫ ወረቀት ዝግጅትና ስርጭት</u>

ቦርዱ፡-

1. ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነት መራጩ በግልፅ ሊረዳው የሚችል እና በተቻለ መጠን የማጭበርበር ተግባርን በሚገባ ለመቀነስና ለመከላከል የሚያስችል የድምፅ መስጫ ወረቀት ያዘጋጃል።
2. በአንድ ጊዜ ለሚከናወኑ ለተለያዩ ምክር ቤቶች ምርጫ የሚያዘጋጀው የድምፅ መስጫ ወረቀት ቀለም የተለያየ ይሆናል።
3. የሚያዘጋጀው የድምጽ መስጫ ወረቀት የእጩዎች ፎቶግራፍ፣ የእጩ መለያ ምልክት፣ የእጩዎች ሙሉ ስምና የፖለቲካ ድርጅታቸው መጠሪያ የታተመበት እንዲሆን ያደርጋል
4. በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ እና በተጨማሪ ለመጠባበቂያ የሚሆን ቁጥሩ በግልፅ በቦርዱ የተወሰነ የመጠባበቂያ የድምፅ መስጫ ወረቀት ይልካል።

### አንቀፅ 13. <u>የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ርክክብና ጥበቃ</u>

1. የምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳው መሰረት ከምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት ሀላፊዎች ለድምፅ መስጫ እለት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን ይረከባሉ።
2. ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራ፥ ለማዳመርና ለውጤት አገላለፅ አገልግሎት የሚሰጡ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከምርጫ ክልሉ ታሽገው በምርጫ ጣቢያው በመጡበት ሁኔታ እስከ ድምፅ መስጫው ዕለት እሽጉ ሳይፈታ፣ ለጥበቃ አስተማማኝ በሆነ እና መቆለፍ በሚችል፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች ብቻ እንዲገቡ በሚፈቀድበት ክፍል ወይም ቦታ በጥንቃቄ መቀመጥ አለባቸው።
3. ከእሽጉ ውጭ ያሉት ለምርጫው አፈፃፀም የሚረዱ የሚለጠፉ ፖስተሮች፣ በራሪ ጽሑፎች፣ ማኑዋሎች፣ ስዕላዊ መግለጫዎች እና የመሳሰሉት በምርጫ ጣቢያው ለተላከለት ዓላማ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።
4. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የቦርዱ የምርጫ ማስፈጸሚያ ቁሳቁሶችና እና ሰነዶች ድልድል፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብና አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 8/2013 ድንጋጌዎችም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ምዕራፍ ሦስት

## <u>የምርጫ ጣቢያ ደህንነትና ሥርዓት አጠባበቅ</u>

### አንቀፅ 14. <u>የምርጫ ጣቢያ ደህንነት</u>

1. የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ 3 ቀን በፊት አስተማማኝ ጥበቃ ተደርጎላቸውና ደኅንነታቸው ተጠብቆ በምርጫ አስፈጻሚዎች መዘጋጀት አለባቸው፤

2. የምርጫ ጣቢያው ደህንነት እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነት በዋናነት የእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ነው፤
3. የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ታዛቢዎች፣ ወይም የእጩ ወኪሎች የምርጫ ጣቢያውን ደህንነት ለመጠበቅ ተጨማሪ የፖሊስ ኃይል እንደሚያስፈልግ ካመኑ የሚመለከተው አካል እንዲመድብላቸው በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አማካይነት ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፤
4. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከታዛቢዎች፣ ወይም ከእጩ ወኪሎች በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የጣቢያውን ደህንነት ለማስከበር ተጨማሪ የፖሊስ ኃይል እንደሚያስፈልግ ሲያምን የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ የምርጫ ጣቢያውንና የአካባቢውን ፀጥታና ደህንነት የሚያስከብሩ የፖሊስ ሀይል እንዲመደቡለት ያደርጋል፤
5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ለምርጫ ጣቢያው የተመደቡት የፖሊስ አባላት በተመደቡበት ቦታ ብቻ እንዲገኙ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ አስፈላጊውን ጥሪ ያደርጋል፤ በተመደቡበት ቦታ በአግባቡ መገኘታቸውንና ተግባራቸውን ለማከናወን ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ ስለሥራቸው ተገቢውን ገለፃ ወዲያውኑ ይሰጣል፤
6. በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ደህንነትና ፀጥታ የሚያስከብሩና በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ጥሪ ሲደረግላቸው ብቻ ወደ ጣቢያው የሚገቡ የፖሊስ ኃይሎች ይመደባሉ፤
7. የፖሊስ አባላት በሀላፊው ጥያቄ ወደ ምርጫ ጣቢያው ከገቡ ተግባራቸውን የሚፈጽሙት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረትና የኃላፊዋን ሕጋዊ ትዕዛዝ በማክበር ይሆናል፤
8. በምርጫ ጣቢያ ወይም በምርጫ ክልል ኃላፊ የምርጫ ደህንነትን የማስከበር ጥያቄ የቀረበለት ማንኛውም የፖሊስ አካል ወይም ሌላ ሰው የመተባበር፣ ፈጣን ምላሽ የመስጠት፥ የማስፈጸም እንዲሁም ተግባሩን እንደፈጸመ ከምርጫ ጣቢያው ወጥቶ ወደ ምድብ ቦታው የመሄድ ግዴታ አለበት፤
9. የምርጫ ጣቢያ ለምርጫ ከመከፈቱም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጋ በኋላ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከዕጩ ወኪሎች፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና ከተፈቀደላቸው ጋዜጠኞች፥ የምርጫ ታዛቢዎች እና ልዩ እንግዶች እንዲሁም እንደአግባብነቱ ከአስተርጓሚዎቻቸው በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም፤
10. በድምጽ መስጫ ሰአታት ከላይ በንኡስ ቁጥር 8 ከተገለጹት ውጪ መራጭ ወይም የመራጭ ረዳት ያልሆኑና ድምጽ የሰጡ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መገኘት የለባቸውም።

## አንቀፅ 15. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

1. ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው 500 ሜትር ዙሪያ መለስ ርቀት ውስጥ በስካር መንፈስ ውስጥ ሆኖ፣ የጦር መሣሪያ ይዞ ወይም በሌላ በማናቸውም ፀጥታን በሚያደፈርስ ሁኔታ ውስጥ መገኘት የለበትም።
2. መራጭ ያልሆኑና ድምፅ የሰጡ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መገኘት የለባቸውም።

3. ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ ወደምርጫ ጣቢያው በመግባት ወይም በምርጫ ጣቢያው ግቢ ውስጥም ሆነ ውጭ የምርጫውን እንቅስቃሴ ማወክ ወይም ማደናቀፍ ወይም ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ እንቅስቃሴ ማድረግ የለበትም።

**አንቀፅ 16. ወደ ምርጫ ጣቢያ የማይገቡ ነገሮች**

1. ማንኛውም ሰው እንደ በራሪ ወረቀት፣ ፖስተር እና በሌሎች አጭር ጽሁፍ መልክ የተዘጋጁ የምርጫ ቅስቀሳ ሰነዶችን ይዞ ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም።
2. ማንኛውም ሰው የጦር መሳሪያ ወይም እንደጩቤና ሴንጢ የመሳሰሉ ስለትነት ያላቸውን ወይም እንደየአካባቢው ሁኔታ ለሀይል መጠቀሚያነት የሚውሉ እንደዱላ፣ አለንጋ ፣ ቁራጭ እንጨት ወይም ብረት ወይም ሌላ ማንኛውንም ተቀጣጣይ ወይም የሚፈነዳ ጠጣር ወይም ፈሳሽ ነገር ይዞ ወደ ምርጫ ጣቢያ መግባት የለበትም።
3. ከላይ የተዘረዘሩትን የተከለከሉ ነገሮች ወደምርጫ ጣቢያ ይዞ የመጣ መራጭ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3)(ለ) መሰረት የምርጫ ጣቢያው የሰልፍ አስከባሪ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት በአደራ አስቀምጦ መግባት አለበት።

# ምዕራፍ አራት

## <u>በድምፅ መስጫ ዕለት በቅድሚያ የሚከናወኑ ተግባራት</u>

**አንቀፅ 17. በድምፅ መስጫ ዕለት ስለሚገኙ ሰዎች**

በድምጽ መስጫ ዕለት፡-

1. የሚከተሉት አካላት ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በቦርዱ በሚገለጽላቸው ሰዓት በጣቢያው መገኘት አለባቸው፡-
   - ሀ) የምርጫ አስፈፃሚዎች
   - ለ) የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት
   - ሐ) የምርጫ ፀጥታ አስከባሪዎች

2. በቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው የሚከተሉት አካላት በጣቢያው መገኘት ይችላሉ፡-
   - ሀ) ታዛቢዎች
   - ለ) የእጩ ወይም የፓርቲ ወኪሎች
   - ሐ) ልዩ እንግዶች

መ) የታዛቢዎች ወይም የልዩ እንግዶች አስተርጓሚዎች (ካሉ)

ሠ) ጋዜጠኞች፡፡

3. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1/ሀ/ የተመለከቱት ሰዎች በእለቱ ካልተገኙና የማይገኙ መሆኑን ካረጋገጠ የምርጫ ጣቢያ ሀላፊው በተጠባባቂነት ከተያዙት ወይም በርዱ በምርጫ ክልሎች ካስቀመጣቸው ተጠባባቂ አስፈጻሚዎች መካከል ምደባ እንዲደረግለት ጠይቆ መተካት አለበት፡፡
4. በምርጫ ክልሉ በተጠባባቂነት የተያዘች ምርጫ አስፈፃሚ ከሌለች ወይም የምርጫ ክልሉ በምርጫ ጣቢያ ሀላፊው ጥያቄ መሰረት የተጓደለችውን የምርጫ አስፈፃሚ ለሟሟላት ካልቻለ የምርጫ ጣቢያ ሀላፊው እራሱን ጨምሮ ቢያንስ ሶስት የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘታቸውን በማረጋገጥ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ጉዳዩ በጣቢያው የማስታወሻ ደብተር ላይ ተመዝግቦ በዕለቱ በተገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች መፈረም ይኖርበታል፡፡
5. በተ.ቁ 4 የተገለፀው ሁኔታ ሲያጋጥም ሐላፊው የስራ ሀላፊነት ሽግሽግ በማድረግ ለተገኙት አስፈፃሚዎች ያሳውቃል፤ውሳኔውንም በተቻለ ፍጥነት ለምርጫ ክልሉ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት በተጓደሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች የተጀመረው የድምፅ አሰጣጥ እየተከናወነ በመደበኛነት ተመልምለው ወይም በተጠባባቂነት ተይዘው የነበሩት ምርጫ አስፈፃሚዎች የተገኙ እንደሆነ በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በሚደረግ ምደባ መሰረት የስራ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ይደረጋል፡፡ የምርጫ ጣቢያ ሀላፊው ሁኔታውን በጣቢያው የማስታወሻ ደብተር ላይ በመመዝገብ ለእጩ ወኪሎችና ታዛቢዎች ስለጉዳዩ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡
7. ከላይ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከቱት ሰዎች ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት ቢበዛ ከንጋቱ 11፡00 ሰአት በምርጫ ጣቢያው ለመገኘት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ዘግይተው ቢመጡም ወደ ምርጫ ጣቢያው ለመግባት ይፈቀድላቸዋል፡፡

## አንቀፅ 18. <u>የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ቁጥጥር</u>

1. የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት እንደ ታሸጉ የተረከበቻቸውን ሰነዶችና ቁሳቁሶች ቀደም ሲል ታሽገው በነበረበት ሁኔታ ፣እሽጉ ሳይፈታ መቆየቱን እንዲሁም በመረካከቢያ ቅጹ ላይ የተመዘገቡትን የማሸጊያ ቁልፍ ቁጥሮች በማመሳከር ለታዛቢዎችና ለእጩ ወኪሎች በግልፅ ታሳያለች፡፡
2. በመረካከቢያ ቅጹ ላይ የተመዘገበው ቁጥር በማሸጊያ ቁልፉ ላይ ካለው የተለየ ከሆነ ወይም የመረካከቢያ ቅጹ ተሰርዞና ተደልዞ ከሆነ ጉዳዩ በምርጫ አስፈጻሚዎችና በእጩ ተወካዮች በቦርዱ በተዘጋጀ ቃለ ጉባኤ ቅጽ ላይ ተመዝግቦ እሽጉ ተፈትቶ ቁሶቹ አንድ ባንድ እንዲቆጠሩ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 19. የመራጮች መዝገብ ቁጥጥር

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የመራጮች መዝገብ: -

1. ምዝገባው ሲጠናቀቅ በቃለጉባኤ ከተያዘው ወይም በምርጫ ሕጉና በቦርዱ የመራጮች ምዝገባ መመሪያ መሠረት በቦርዱ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተመዘገበችው የመጨረሻ ተመዝጋቢ መለያ ቁጥር ውጭ አዲስ ተመዝጋቢ ያልተመዘገበባቸው መሆኑን በሰአቱ ለተገኙ ታዛቢዎችና የእጩ ወኪሎች በግልፅ ታሳያለች።
2. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ካደረገች በኋላ የመራጮችን መዝገብ ለመዝገብ ሹሚ ትሰጣለች።

## አንቀፅ 20. ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ስለሚደረግ ጥንቃቄና ቁጥጥር

የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ለእያንዳንዱ ምርጫ የተረከባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀት ጥራዝ እሽጎች ላይ ያሉ የመጀመሪያና የመጨረሻ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች መለያ ቁጥር ከመረካከቢያ ቅጹ ጋር በማመሳከር በእያንዳንዱ የምርጫ ዓይነት የውጤት ማመሳከሪያ እና ማሳወቂያ ቅጽ ላይ ለጣቢያው የደረሰውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት ይመዘግባል።

## አንቀፅ 21. የድምፅ መስጫ ሳጥን እና የሳጥን ማሸጊያ ቁልፍ ቁጥጥር

የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ: -

1. ለእያንዳንዱ የምርጫ ዓይነት የድምፅ መስጫ ሳጥኖችን ማሸጊያ ያዘጋጃል።
2. የድምፅ መስጫ ሳጥኑ ባዶ መሆኑን በምርጫ አስፈጻሚዎች፣ የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትና ታዛቢዎች ፊት በማቅረብ በውስጡ ምንም ነገር የሌለ መሆኑ እንዲረጋገጥ ያደርጋል።
3. ባዶ መሆኑ የተረጋገጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን መለያ ቁጥራቸው በድምጽ መስጫ ሳጥን ማሸጊያዎች መመዝገቢያ ቅጽ ላይ በተመዘገቡ ማሸጊያዎች የጎኑ ቀዳዳዎች በግልፅ እንዲዘጉ ያደርጋል፤ ይህንኑ ሂደት በእያንዳንዱ ተጨማሪ የድምጽ መስጫ ሳጥን ላይ ይፈጽማል። የድምፅ መስጫ ሳጥን ማሸጊያ መለያ ቁጥሮችን የእጩ ወኪሎችና ታዛቢዎች መዝግበው እንዲይዙ ሊያደርግ ይችላል።
4. የድምፅ መስጫ ሳጥኑ ለመራጮች፣ ለታዛቢዎችና ለእጩ ወኪሎች ፊት ለፊት በግልፅ ሊታይ በሚችልበት ሁኔታ በተዘጋጀው ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ያደርጋል።

## አንቀፅ 22. <u>የሌሎች ቁሳቁሶች ዝግጅት</u>

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለመዝገብ ሹሞች እስክሪብቶ፣ የመፈረሚያ ቀለምና ድምጽ በሰጡ መራጮች ጣት ላይ የሚቀባ የማይለቅ ቀለምና በአጠቃላይ አስፈላጊ ቁሳቁሶች መሰጠቱን እንዲሁም በሚስጥር ድምፅ መስጫ ክፍል ውስጥ እስክሪብቶና የመፈረሚያ ቀለም መቀመጣቸውን ያረጋግጣል፡፡

## አንቀፅ 23. <u>ዝግጅት መጠናቀቁን ይፋ ስለማድረግ</u>

1. በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱት የዝግጅት ተግባራት በህጉ መሠረት መፈፀማቸውን እና በምርጫ ጣቢያው ድምፅ አሰጣጡን ለመጀመር የሚያስችል መሆኑ በርዱ ባዘጋጀው መክፈቻ ቃለጉባኤ ቅፅ ላይ ከተመዘገበ በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች ይፈርማሉ፤ ታዛቢዎችና የእጩ ወኪሎችም ሊፈርሙ ይችላሉ፡፡
2. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የምርጫ ጣቢያው መከፈቱንና የድምፅ አሰጣጡ መጀመሩን ድምፅ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ለሚገኙ መራጮች በይፋ ያሳውቃል፡፡
3. በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት የተመዘገቡ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች፣ ታዛቢዎች፣ የእጩ ወኪሎች ፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፥ ጋዜጠኞችና ለምርጫ ጣቢያው የተመደቡ ፖሊሶች ቀድመው እንዲመርጡ ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# <u>የድምፅ አሰጣጥ መጀመር</u>

## አንቀፅ 24. <u>ወደ ምርጫ ጣቢያው ስለሚገባበት ሥርዓት</u>

1. የሰልፍ አስከባሪው መራጮችን የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዳቸውን በመመልከት በምርጫ ጣቢያው የተመዘገቡ መሆናቸውን እንዲሁም የድምጽ ሰጪነት የቀለም ምልክት የሌላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አጭር ገለፃ ወደሚደረግበት ስፍራ ይመራቸዋል።
2. ገለፃ ለማድረጊያ በተዘጋጀው ቦታ በምርጫ ጣቢያ ሀላፊው መራጮች የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹን ዓይነት፣ ቀለም፣ በእስክሪብቶ ወይም በጣት አሻራ ምልክት እንዴት እንደሚደረግ፣ ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነት ምን ያህል እጩዎች መምረጥ እንደሚቻልና ድምፅ የሚሰጠው በሚስጢር ክፍል መሆኑን በሚመለከት የሚሰጠውን ገለፃ እንዲከታተሉ ይደረጋል።

**አንቀፅ 25. <u>ድምፅ ለመስጠት ብቁ ስለመሆን</u>**

1. ድምፅ ለመስጠት በተመዘገበችበት የምርጫ ጣቢያ የተገኘች መራጭ፡-
   ሀ) የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ያላት፣
   ለ) የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያ ወይም በመራጮች ምዝገባ ወቅት የተረጋገጠበት ሌላ ሰነድ ያላት፣ወይም ማንነቱዋ በምርጫ ምዝገባ ወቅት በምስክሮች ስለመረጋገጡ በመራቾች መዝገብ ላይ የሰፈረላት፣
   ሐ) የመራጮች መዝገብ ላይ ስሟ የሰፈረ፣
   መ) ድምፅ ያልሰጠች መሆኑ ሲረጋገጥ ድምጿን የመስጠት መብት አላት።

2. የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ የጠፋባት መራጭ ጉዳዩን ለምርጫ ጣቢያው በማስረዳት ማንነቷ እንዲሁም በመዝገቡ ላይ ስሟ የሰፈረና ያልመረጠች መሆኑ ሲረጋገጥ ጉዳዩ በቃለ ጉባኤ ተይዞ እንድትመርጥ ይደረጋል።

**አንቀፅ 26. <u>ድጋፍ ስለሚፈልጉና ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው መራጮች</u>**

1. የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ነፍሰጡሮችን፣ ጨቅላ ህጻናት የያዙ ወላጆችን፣ መለዮ የለበሱ የመከላከያና የፖሊስ አባላትን ቅድሚያ በመስጠት ድምፅ እንዲሰጡ ማድረግ አለበት።
2. በድምፅ አሰጣጡ ሂደት ምልክት ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደሳጥን ለመክተት እገዛ የሚያስፈልገው መራጭ ራሱ የመረጠውን ሰው ይዞ የመምጣት መብት አለው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በድጋፍ ፈላጊው የሚመረጥ ሰው :-
   ሀ) ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ መሆን አለበት።
   ለ) እጩ ተወዳዳሪ ወይም የእጩ ወኪል መሆን የለበትም።
4. አንድ ድጋፍ የሚሰጥ ሰው ከአንድ በላይ መራጭ ለመደገፍ አይችልም፡፡
5. ድጋፍ የሚያስፈልገው መራጭ ራሱ የመረጠውን ሰው ይዞ ያልመጣ እንደሆነ ምልክት ለማድረግ እንዲሁም የድምፅ መስጫ ወረቀት ወደ ሳጥን ለመክተት አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ የሚሰጠው የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ብቻ ነው።

**አንቀፅ 27. <u>የመራጩን ማንነትና ምዝገባን ስለማጣራት እና የድምፅ ሰጭነት ቀለምን ስለመቀባት</u>**

1. ማንኛውም መራጭ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱን እና የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ ለተመዘገበበት ምርጫ ጣቢያ የመዝገብ ሹም በማቅረብ ስሙ በመዝገቡ ላይ እንዲታይለት ይጠይቃል።
2. የመዝገብ ሹሙ የሚከተሉትን ማጣራት ይኖርበታል፤

ሀ) የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱ በምርጫ ጣቢያው የተሰጠ መሆኑን፣

ለ) የመራጩን ማንነት የሚያረጋግጥ መታወቂያ ወይም መለያ ወረቀት አብሮ የቀረበ መሆኑን፣

ሐ) በካርዱ ላይ በተመዘገበው የመዝገብ ገጽ እና ተራ ቁጥር እንዲሁም የመራጭ መለያ ቁጥር መሰረት ሙሉ ስሙ በመዝገቡ ላይ በትክክል የሰፈረ መሆኑና፣

መ) የድምጽ ሰጪነት ቀለም ያልተቀባ መሆኑን።

3. የመዝገብ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከቱት መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ መራጯ ድምጽ የሰጠች መሆኑን ለማመልከት ከድምፅ መስጫ ወረቀት አዳዩ ድምፅ መስጫ ወረቀት ከመቀበሏ አስቀድሞ በግራ እጅ አውራጣቷ ጥፍር ግርጌ፣ የግራ አወራጣት ከሌላት በሌላ ማናቸውም የግራ እጅ ጣት፣ማናቸውም የግራ እጅ ጣት ከሌላት በቀኝ አውራጣት ግርጌ ይህም ከሌለ በማናቸውም ሌሎች የቀኝ እጅ ጣት ጥፍሯ ግርጌ ላይ የማይለቅ ቀለም ይቀባታል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) የተጠቀሰው ቢኖርም መራጩ የእጅ ጣት የሌለው ከሆነ የመዝገብ ሹሙ አለመምረጡን ካረጋገጠ በኋላ ከመራጩ ጋር በመስማማት በቀላሉ የሚታይ በታ ላይ የማይለቅ ቀለም ይቀባና እንዲመርጥ ያደርጋል።
5. ከላይ በንዑስ ቁጥር 3 እና 4 በተደነገገው መሰረት መራጩ የማይለቅ ቀለም ከተቀባ በኋላ የምርጫ አስፈጻሚው በመራጭ መዝገብ ላይ ለዚሁ በተዘጋጀው አምድ ላይ መራጩ እንዲፈርም ያደርጋል።
6. የእጆቹን ጣቶች ለምርጫ አስፈፃሚው ለማሳየት ወይም ቀለም ለመቀባት ፈቃደኛ ያልሆነ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት አይሰጠውም፣ መምረጥም አይችልም።
7. ድጋፍ ለሚፈልጉ መራጮች ድጋፍ ለመስጠት አብረው የመጡ ሰዎች ድምፅ የሚሰጡ ካልሆነ በስተቀር ጣታቸውን ቀለም አይቀቡም።

## **አንቀፅ 28. የድምፅ መስጫ ወረቀት ስለመስጠት**

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 መሠረት ተገቢው ሂደት ከተፈፀመ በኋላ ለመራጩ ለምርጫ ጣቢያው ከተዘጋጀው የድምፅ መስጫ ወረቀት ለአንድ ምክር ቤት አንድ የድምፅ መስጫ ወረቀት በድምፅ መስጫ ወረቀት አዳዩ አማካይነት ይሰጠዋል።
2. በዕለቱ የሚካሄደው ምርጫ ከአንድ በላይ ለሆኑ ምክር ቤቶች ሲሆን ለየምክር ቤቱ ምርጫ አንድ አንድ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ይሰጠዋል።
3. የድምፅ መስጫ ወረቀት አዳይ  የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ከጥራዙ ላይ በመነጠል ለየምክር ቤቱ የተዘጋጀውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በጀርባው ላይ ማህተም በማድረግ ለመራጩ በመስጠት የትኛውን የድምጽ መስጫ ወረቀት የትኛው ሣጥን ውስጥ መክተት እንዳለበት ገለልተኛ በሆነ አኳኋን ያስረዳል።

### **አንቀፅ 29.** <u>**ወደ ሚስጥር ክፍል ስለመግባት**</u>

1. የድምፅ መስጫ ወረቀቱን የተቀበለ መራጭ ለዚሁ በተዘጋጀው ከማንም እይታ በተከለለው የሚስጥር ቦታ በመግባት በሚስጥር ድምፅ ይሰጣል።
2. ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው መራጮች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 27 መሠረት ከመረጧቸው ሰዎች ጋር ወደ ሚስጥር ክፍል በመግባት ድምፅ ይሰጣሉ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) እና በአንቀፅ 27(5) ላይ ከተጠቀሰው በስተቀር መራጩ ወደ ሚስጥር ድምፅ መስጫው ገብቶ ድምፅ በመስጠት ላይ እያለ ማንም ሰው በምንም ሁኔታ ተከትሎ ወይም ተደርቦ መግባት ወይም ወደ ሚስጥራዊው ቦታ መጠጋት አይችልም።
4. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እና በቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው የእጩ ወኪሎችና ታዛቢዎች የሚስጥር ድምፅ መስጫ ቦታ ላይ የተቀመጡ እስክሪብቶ እና መርገጫዎች በተገቢው ሁኔታ መኖራቸውን እና ሌሎች የተከለከሉ የቅስቀሳ ጽሑፎች አለመለጠፋቸውን ወይም አለመቀመጣቸውን መራጮች ድምፅ በማይሰጡበት ክፍተት በየተወሰነ ጊዜ እየገቡ ያረጋግጣሉ።

### **አንቀፅ 30.** <u>**የድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ ድምፅ መስጫ ወረቀት ስለመክተት**</u>

1. መራጩ በአግባቡ ድምፅ የሰጠበትን የድምፅ መስጫ ወረቀት በቁመቱ ወደ ውስጥ በማጠፍ በምርጫ አስፈጻሚዎች፣ የእጩ ወኪሎች ፣ እንዲሁም በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ ዕይታ በግልፅ ስፍራ በተቀመጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ በመክተት ከምርጫ ጣቢያው ይወጣል።
2. በምርጫ ጣቢያው የተመደበው የድምፅ መስጫ ሣጥን ተቆጣጣሪ መራጮች የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን መራጮች በትክክለኛው የድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ወረቀቱን መክተታቸውንና ከጣቢያው ይዘው አለመውጣታቸውን በመከታተል ያረጋግጣል።

### **አንቀፅ 31.** <u>**ስለተበላሸ የድምፅ መስጫ ወረቀት**</u>

1. መራጩ የተሰጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በአግባቡ ሳይጠቀምበት ቀርቶ የተበላሸበት እንደሆነ ሁኔታውን ለድምፅ መስጫ ወረቀት አዳይ በማስረዳት ሌላ የድምፅ መስጫ ወረቀት እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል።
2. የድምፅ መስጫ ወረቀት አዳዩም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰውን የተበላሸ የድምፅ መስጫ ወረቀት የፊት ገጽ ሳይመለከት እንዲመለስ በማድረግ በጀርባው ላይ ***«የተበላሸ»*** የሚል ምልክት አድርጎ የተበላሸውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ለዚሁ ተግባርና የምርጫ ዓይነት በተዘጋጀው ***"የተበላሹ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች"*** *ፖ*ስታ/ኤንቨሎፕ ውስጥ ይከታል።

## አንቀፅ 32. <u>ድምፅ የመስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑ</u>

1. ድምፅ የመስጠት ሂደት ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም።
2. የምርጫ ጣቢያው ኋላፊ የምርጫ ጣቢያው በሁከት፣ ግጭት፣ በአውሎ ንፋስ፣ በጎርፍ፣ በእሳት ወይም በማንኛውም አስገዳጅ ምክንያት ድምፅ መስጠት እና የቆጠራ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ የማይቻልበት ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ካጋጠመው ከሌሎች ምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር በመሆን የድምፅ መስጠት ሂደቱ እንዲቋረጥ ሊወስን ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ከላይ በተጠቀሱት አስገዳጅ ምክንያቶች ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ከተቋረጠ፡-

   ሀ) የድምፅ አሰጣጡን ሂደት እንዲቋረጥ ያደረገው አስገዳጅ ሁኔታ መስተካከሉ በምርጫ አስፈጻሚዎች ከታመነበት፣ እና

   ለ) ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ከተያዘ በኋላ የተቋረጠው ድምፅ የመስጠት ሂደት ሊቀጥል ይችላል።

4. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት የተቋረጠበት በንዑስ ቁጥር 2 ስር የተመለከተው ከአቅም በላይ የሆነው ሁኔታ ሊስተካከል እንደማይችል ከተረጋገጠ ሰነዶቹና ቁሳቁሶቹ በተቀመጠው አሰራር መሰረት ታሽገውና ጥበቃ ተደርጎላቸው ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ባለበት እንዲቆም ይደረጋል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው አጠቃላይ ሁኔታ ለበላይ የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ወይም እንደሁኔታው ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ይደረጋል።
6. ከላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች አግባብ የተቋረጠው የድምፅ መስጠት ሂደት፥ ቦርዱ እንደአግባብነቱ በሚወስነው መሠረት መደበኛው የድምፅ መስጫ ሰዓት ማጠናቀቂያ እንዲራዘም ተደርጎ እንዲከናወን ወይም በሌላ ጊዜ እንዲካሄድ ይደረጋል።

## አንቀፅ 33. <u>ድምፅ መስጠትን ስለመቃወም</u>

1. ለማንኛውም መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት፣ ድምፅ በመስጠት ሂደት ላይ ያለው ሰው ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ወይም በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት ያልተመዘገበ ነው በማለት የእጩ ተወካይ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል።
2. አንድ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ሲከለከል ደግሞ ራሱ ወይም ከእጩ ተወካዮች አንዱ ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል።
3. የእጩ ተወካይ ወይም መራጩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ከተደነገጉት መቃወሚያ ነጥቦች ውጭ በሆነ ምክንያት በማንኛውም የምርጫ አስፈፃሚ፣ የእጩ ተወካይ ወይም በሌላ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በተገኘ ሰው አግባብ ያልሆነ ድርጊት ተፈፅሞብኛል በማለት ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል።

4. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ቅሬታዎች የሚቀርቡት ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ነው፤ ኮሚቴው የቀረበውን ቅሬታ ከተመለከተ በኋላ ቅሬታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል የድምጽ መስጫው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት በቦርዱ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት በጽሁፍ ውሳኔውን ያሳውቃል።
5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በዚህ አንቀፅ መሠረት የቀረቡ ቅሬታዎችንና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ ውሳኔዎችን የጽሁፍ ሰነድ ግልባጭ በመረጃነት ይይዛል።

**አንቀፅ 34. <u>ስለጊዜያዊ ድምፅ</u>**

1. በአዋጁ አንቀጽ 54 እና 154 እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 35 መሠረት አንድ ሰው ድምፅ መስጠት የለበትም የሚል ተቃውሞ ሲቀርብለት፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው፡

   ሀ) ጉዳዩን ካጣራ በኋላ ተቃውሞውን ውድቅ በማድረግ መራጩ ድምጽ እንዲሰጥ ሊፈቅድለት፣ ወይም

   ለ) ተቃውሞ የቀረበበት ሰው ላይ የቀረበበው አቤቱታ አሳማኝ ቢሆንም መራጩ ይግባኝ እስከሚል ጊዜያዊ ድምፅ መስጠት አለበት ብሎ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ካመነ፥ መራጩ ለዚሁ በተዘጋጀው ፖስታ የሚቀመጥ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ ይደረጋል፤ ይህም ሁኔታ ***"አስተያየት"*** በሚለው የመራጮች መዝገብ አምድ ላይ መስፈር አለበት።

2. ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ የተፈቀደለት መራጭ  በሚስጥር ድምፅ መስጫ ክፍል በመግባት ድምፁን እንዲሰጥ ከተደረገ በኋላ የድምፅ መስጫ ወረቀቱን በፖስታ አሽጎ በማምጣት የምርጫ ጣቢያው መለያ ኮድ እና የመራጩ አድራሻ የተፃፈበት ሌላ ፖስታ ውስጥ ገብቶ ፖስታው ከታሸገ በኋላ የድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ ይከተታል።
3. የተሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ በምርጫ ሕጉ መሰረት የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ስልጣን ላለው ለወረዳ ፍርድ ቤት ወይም በአዲስ አበባና በድሬዳዋ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መራጩ መምረጥ መብት እንዳለው በሚሰጠው ውሣኔ መሰረት በቆጠራ ሊካተት ወይም ውድቅ ሊደረግ ይችላል።
4. ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ስልጣን ካለው አካል የመምረጥ መብት ያለው መሆኑን በምርጫ ክልሉ የድምፅ ማዳመር ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል።
5. የምርጫ ጣቢያ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንደሚመራ እንዲሁም መራጩ ውሳኔውን ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ማስረከብ ያለበት የድምፅ ማዳመር ከመጠናቀቁ በፊት እንደሆነ ለመራጩ ማሳወቅ አለበት።
6. በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሰረት ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ስልጣን ላለው ለወረዳ ፍርድ ቤት ወይም

በአዲስ አበባና በድሬዳዋ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱም ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ የድምጽ ማዳመሩ ሂደት እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል።

# ምዕራፍ ስድስት

## ስለድምፅ አሰጣጥ መጠናቀቅ

### አንቀፅ 35. የምርጫ ጣቢያ መዘጋት

1. የድምፅ መስጫው ሰዓት ሲጠናቀቅ የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ የምርጫ ጣቢያ እንዲዘጋ ያደርጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም የምርጫ ጣቢያው ሲዘጋ በሰልፍ ላይ ሆነው ተራ ሲጠብቁ የነበሩ መራጮች ድምፅ እንዲሰጡ መደረግ አለበት።
3. የምርጫ ጣቢያው ከተዘጋ በኋላ ከምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ፣ ከዕጩ ወኪሎች፣ ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው ጋዜጠኞች፥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፥ ከታዛቢዎች እና ልዩ እንግዶች እና አስተርጓሚዎቻቸው በስተቀር ማንም ሰው ወደምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም።
4. የምርጫ ጣቢያው ፀጥታ አስከባሪዎች በመግቢያው በር ላይ በመሆን ጥበቃ ያደርጋሉ።

### አንቀፅ 36. የድምፅ መስጫ ሳጥን ስለመቆለፍ እና ስለሚደረግ ጥንቃቄ

1. የመጨረሻው መራጭ ድምጽ እንደሰጠ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፣

   ሀ) የምርጫ አስፈፃሚዎች

   ለ) የአገር ውስጥ ታዛቢዎች፣

   ሐ) የዕጩ ወይም የፓርቲ ወኪሎች፣

   መ) ልዩ እንግዶች፣

   ሠ) ከቦርዱ ባጅ የተሰጣቸው የዐለም አቀፍ ታዛቢዎች ወይም የልዩ እንግዶች አስተርጓሚዎች (ካሏቸው) እና

   የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ባሉበትና በግልፅ በሚያዩበት ሁኔታ የድምጽ መስጫ ሳጥኑ ከተቀመጠበት ሳይነሳ የላይኛውን የሳጥኑን ቀዳዳ መለያ ቁጥር ባለው ማሸጊያ ያሸገዋል።

2. ሳጥኑ የታሸገበት ማሸጊያ ቁጥር ለዚህ በተዘጋጀው የድምፅ ሳጥን ማሸጊያ ቁጥሮች መመዝገቢያ ቅጽ ላይ እንዲመዘገብ ይደረጋል።
3. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት የውሎ ሁኔታ በዝርዝር ተገልፆ በጣቢያው የማስታወሻ ደብተር እንዲያዝ እና በቦታው የተገኙ የእጩ ወኪሎችና እና ታዛቢዎች እንዲፈርሙበት ይደረጋል።

4. በሂደቱ ሁሉ ለድምፅ መስጫ ሳጥኑና ለሌሎች የምርጫ ቁሳቁሶች አስፈላጊው ጥበቃና ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ

### አንቀፅ 37. የድምፅ ቆጠራ ቦታ

1. በማንኛውም ምርጫ የድምፅ ቆጠራ የሚከናወነው ድምፅ በተሰጠበት የምርጫ ጣቢያ ድምጽ መስጠት እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም በጸጥታ መደፍረስ ወይም ቆጠራው ቢካሄድ በጣቢያው በተገኙ ሰዎች፤ በድምጽ መስጫ ወረቀቶች ደህንነት፤ ወይም በቆጠራው ሂደትና ውጤት ላይ ችግር ሊያስከትል በሚችል ተመሳሳይ አስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት: -
   ሀ) በምርጫ ጣቢያው ቆጠራ ለማካሄድ የማይቻል ከሆነ የተፈጠረውን አስገዳጅ ሁኔታ የምርጫ ጣቢያው ለምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት በመግለፅ ጥያቄ ሲያቀርብ እና
   ለ) የምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ሲፈቅድ፣ ወይም
   ሐ) የምርጫ ክልሉ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ ሲወስን፣

ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ሊካሄድ ይችላል።

3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራው በምርጫ ክልሉ እንዲካሄድ ያስፈለገበትን ምክንያት በመግለፅ ጥያቄውን ለምርጫ ክልሉ የሚያቀርበው በምርጫ ጣቢያው ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ውሣኔ መሆን አለበት።
4. የምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2)(ሐ) የተመለከተውን ውሣኔ የሚሰጠው በምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ጋር በመሆን ይሆናል።
5. የቆጠራ ቦታ ለመለወጥ የተደረጉት ስብሰባዎች ቃለጉባኤ ተይዞ ለበላይ የምርጫ ጽሕፈት ቤት ሪፖርት መደረግ አለበት።
6. የድምፅ ቆጠራ በምርጫ ክልል ፅ/ቤት እንዲካሄድ ሲወሰን ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ሰነዶችና ቁሳቁሶች የሚታሸጉትና የሚጓጓዙት በቦርዱ የምርጫ ማስፈጸሚያ ቁሳቁሶችና እና ሰነዶች ድልድል፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብና አወጋገድ መመሪያ መሰረት መሆን አለበት።
7. በምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ቆጠራው የሚደረገው በምርጫ ጣቢያው የነበሩት የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ታዛቢዎች በምርጫ ክልሉ በተገኙበት መሆን አለበት።
8. ከላይ የተደነገገው ቢኖርም የምርጫ ጣቢያው የእጩ ወኪሎች በራሳቸው ምክንያት ያልተገኙ እንደሆነ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ በምርጫ ክልሉ ተመድበው በተገኙት የእጩ ወኪሎች ተተክተው፣ ካልተገኙ

ደግሞ በሌሉበት ሂደቱ እንዲቀጥል ይደረጋል፤ እንዲሁም ባልተገኙበት ወቅት የሚከናወን ቆጠራ ውድቅ እንዲደረግ ሲሉ ለመጠየቅ አይችሉም።

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) የተደነገገው ቢኖርም ወኪሉ ያልተገኘው ሆን ተብሎ በተቀነባበረ መሰናክል ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ወኪሉ ሳይኖር የተከናወኑ የምርጫ ተግባራት ወኪሉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት እንደአግባብነቱ በምርጫ ክልሉ ወይም በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል።
10. የድምጽ ቆጠራ በምርጫ ክልል ፅ/ቤት እንዲከናወን ሲወሰን የምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በምርጫ ክልሉ እንዲገኙ ቦርዱ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል።
11. የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ጨምሮ የድምፅ ቆጠራውን በዚህ መመሪያ መሰረት በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ያከናውናሉ።
12. በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ከአንድ በላይ የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራ የሚከናወን ከሆነ እንደ አመጣጣቸው ወይም የምርጫ ክልሉ ኃላፊ ከምርጫ ጣቢያው ኃላፊዎች ጋር በመስማማት በሚወስነው ሌላ ቅደም ተከተል መሠረት ይከናወናል።
13. የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ ቆጠራው አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር ሊሰጡ ይችላሉ።

## አንቀፅ 38. <u>የድምፅ መቁጠሪያ ቦታ ስለማዘጋጀት</u>

1. የድምፅ መቁጠሪያ ቦታው የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ታዛቢዎች ተገኝተው በቅርበት እያዩ ለመከታተል በሚችሉበት ሁኔታ በቂ ብርሃን ያለበት ምቹ ቦታ ሆኖ በምርጫ አስፈፃሚዎች ተመርጦ ይዘጋጃል።
2. ባስገዳጅ ሁኔታ የድምጽ መቁጠሪያው ቦታ በምርጫ ክልሉ ትእዛዝ የተቀየረ እንደሆነ የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትና ታዛቢዎች በቆጠራው ቦታ እንዲገኙ የምርጫ ጣቢያ ሀላፊው የቆጠራውን ቦታ እና ሰዓቱን እንዲያውቁት ያደርጋል።
3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፣ የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ከሚቴ አባላት እና የምርጫ ታዛቢዎች ባሉበት የድምፅ መስጫውን ሳጥን ከተቀመጠበት ቦታ በጥንቃቄ በማንሳት ለሁሉም በሚታይ መልኩ ለቆጠራ በተዘጋጀው ቦታ ያስቀምጣል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት ቆጠራ ለመጀመር የሚያስችል በቂ ብርሃን የሌለ እንደሆነ የእጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ይህንኑ በመግለጽ ቃለጉባኤ ይፈራረማሉ። ይህም ሲሆን ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶችና ሌሎች ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ቁሳቁሶችና ሰነዶች አስፈላጊው የጥበቃ ኃይል እንዲኖር በማድረግ ደህንነታቸው በተረጋገጠ ሁኔታ እንዲያድሩ መደረግ አለበት። በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተጠቀሱት ሰዎች ከፈለጉ በምርጫ ጣቢያው መቆየት ይችላሉ።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት የተቋረጠ የድምጽ ቆጠራ ሂደት በሚቀጥለው ቀን እጅግ ቢዘገይ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል።

**አንቀፅ 39. የድምፅ መቁጠሪያ ሰነድ እና ቁሳቁስ ስለማዘጋጀት**

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለቆጠራው ተግባር ከቦርዱ የተቀበላቸውን የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ፣ የድምፅ መቁጠሪያ ሰንጠረዥ ፣ እስክሪቢቶ እና ምርጫ ጣቢያው ከተቋቋመበት ተቋም ወይም በአካባቢው ካለ የመንግስት መስሪያ ቤት በውሰት የወሰደውን ጠረጴዛ ለቆጠራ ዝግጁ ያደርጋል።

**አንቀፅ 40. ስለድምፅ ቆጠራው አፈፃፀም ገለፃ ስለመስጠት**

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ስለድምፅ ቆጠራው አፈፃፀም ለምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ለእጩ ወኪሎች፣ ለምርጫ ታዛቢዎች እና ለየቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ገለፃ ይሰጣል። ገለፃውም የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ማብራራት አለበት፦

1. ቆጠራው ከድምጽ መስጫ ሳጥን ውጪ ያሉትን አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የተበላሹ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ እና ከሳጥን ውጪ ወድቀው የተገኙ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን በመቁጠር እንደሚጀመር፣ በመቀጠልም ድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ ያሉት ወረቀቶች ይቆጠራል፤
2. በጠቅላላ ምርጫ መጀመሪያ የሚቆጠረው ድምጽ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆኖ በመቀጠል የክልል ምክር ቤት ድምጽ እንደሚቆጠር። ህዝበ ውሳኔ የሚደረግ ከሆነም የዚሁ ቆጠራ ከክልል ምክር ቤት ቆጠራ በኋላ ይደረጋል፤
3. የድምጽ ማመሳከር ሂደት ከድምጽ መስጫ ሳጥኑ ውጪ ያሉት እና በድምጽ መስጫ ሳጥኑ ውስጥ የተገኙት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ድምር ጣቢያው ከተረከባቸው ጠቅላላ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ጋር እኩል መሆኑን የሚመሳከርበት ሂደት ነው፤
4. በተጨማሪም የድምጽ ማመሳከሩ ሂደት ለጣቢያው የደረሰውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ድምር ድምጽ ከሰጡ መራጮች ቁጥር፣ ከተበላሹ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቁጥር፣ ከሳጥን ውጪ ወድቀው የተገኙ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቁጥር እና በጊዜያዊነት ከተሰጡ ድምጾች ቁጥር ጋር ማመሳከርንም ያካትታል፤
5. ሁለቱ አይነት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከተመሳከሩ በኋላ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጡ ድምጾች፤
   
   ሀ) በተሰጡለት እጩ ይለያሉ፣
   
   ለ) በተሰጡለት እጩ ይቆጠራሉ፣
   
   ሐ) ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠው ድምጽ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተዘጋጀው የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይሞላሉ፣

መ) በድምጽ ቆጠራው ጊዜ የተገኙት ዋጋ አልባ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተዘጋጀው የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይሞላሉ፡፡

6. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተለይተው ተቆጥረው ካለቁ በኋላ ከአንድ የምርጫ ክልል ከአንድ በላይ እጩዎች የሚመረጡባቸው የክልል ምክር ቤቶች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፤

   ሀ) አንድ በአንድ ተከፍተው ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠ ድምጽ በውጤት መቁጠሪያ ቅጽ ላይ ይመዘገባል፣

   ለ) በውጤት መቁጠሪያው ቅጽ ላይ ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠው ጠቅላላ ድምጽ ተደምሮ ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በተዘጋጀው የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘገባል፣

   ሐ) በድምጽ ቆጠራው ጊዜ የተገኙት ዋጋ አልባ ድምፆች ተቆጥረው ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በተዘጋጀው የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይሞላሉ፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ የምርጫ ክልል አንድ እጩ ብቻ የሚመረጥባቸው የክልል ምክር ቤቶች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የሚቆጠሩት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) ስለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተደነገገው መሰረት ይሆናል፤
8. ከአንድ ምርጫ ክልል አንድ እጩ ብቻ የሚመረጥባቸው የአካባቢ ምርጫዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የሚቆጠሩት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) ስለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተደነገገው መሰረት ሲሆን፣ ከአንድ በላይ እጩዎች የሚመረጡባቸው የአካባቢ ምርጫዎች ደግሞ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) ከአንድ በላይ እጩዎች የሚመረጡባቸው የክልል ምክር ቤቶች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በሚቆጠሩበት ስርዓት ይሆናል፤
9. ለህዝበ ውሳኔ ድምፅ ቆጠራ በዚህ አንቀፅ ንኡስ ቁጥር 4 ላይ ለህዝብ ተወካዮች የተሰጡ ድምፆች አቆጣጠር ሂደት እንደ አግባብነቱ ተግባራዊ ይደረጋል፤
10. ስለ ድምጽ አቆጣጠር የሚሰጠው ገለጻ የምርጫ ጣቢያው የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ በምርጫ ጣቢያው ለህዝብ ይፋ የሚደረግ መሆኑንም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 41. ድምፅ የሰጡ መራጮችን ብዛት እንዲሁም ከድምፅ መስጫ ሳጥኑ ውጪ ያሉ ድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ስለመቁጠር

1. የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የማመሳከር ስራ በመራጮች መዝገብ ላይ የድምፅ መስጫው ዕለት የመራጩ ፊርማ በሚለው አምድ ስር የፈረሙትን ድምፅ የሰጡ መራጮች አንድ በአንድ በግልፅ በመቁጠርና በማዳመር ቁጥሩ በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ እንዲመዘገብ በማድረግ ይከናወናል፡፡
2. በዕለቱ በጥቅም ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረው በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘገባሉ፡፡

3. በዕለቱ የተበላሹ (የተበላሹ ድምፅ መስጫ ወረቀቶች) የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረው በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘገባሉ፡፡
4. በዕለቱ ከድምፅ መስጫ ሳጥን ውጪ ወድቀው የተገኙ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረው በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘገባሉ፡፡
5. በዚህ አንቀፅ የተመለከቱት ተግባራት የሚከናወኑት በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ተቆጣጣሪነት በምርጫ አስፈጻሚዎች ሆኖ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም በጣቢያው የተገኙ የዕጩ ወኪሎች፣ ታዛቢዎችና ጋዜጠኞች በግልፅ በሚያዩበት ሂደት ይሆናል፡፡
6. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፤
   ሀ) የምርጫ ጣቢያው የተቀበላቸውን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣
   ለ) በመራጮች መዝገብ ላይ የሰፈሩትን ፊርማና የጣት አሻራ ብዛት፣
   ሐ) የተበላሸውን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣
   መ) ከሳጥን ውጪ ወድቀው የተገኙ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣
   ሠ) አገልግሎት ላይ ያልዋለውን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፡፡

እንዲመዘገብ በማድረግ በይፋ መግለፅ አለበት፡፡

7. ከዚህ በላይ የተዘረዘረው የቁጥጥር ሂደት ምርጫው ከአንድ በላይ ለሆኑ ምክር ቤቶች እንዲሁም ህዝበ ውሳኔን አካቶ የሚካሄድ ሲሆን ለየምክር ቤቱና ለህዝበ ውሳኔ የተላኩት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለየብቻ ተቆጥረው በየተራ ለእያንዳንዱ የምርጫ ዓይነት በተዘጋጀ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## <u>ስለድምፅ ቆጠራ</u>

### አንቀፅ 42. <u>በድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ ያሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ስለመቁጠር</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 ሥር የተዘረዘሩት ተግባራት ከተፈጸሙ በኋላ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፡-
   ሀ) የድምጽ መስጫ ሳጥኑ ማሸጊያዎች ተሰብረው ያልተከፈቱ መሆናቸውን ከተገቢው ቅጽ ጋር በማመሳከር ያረጋግጣል፣ ሂደቱንም የእጩ ወኪሎችና እውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎች በሚገባ እንዲመለከቱት ያደርጋል፤
   ለ) ከዚያም የላይኛውን የድምጽ መስጫ ሳጥን ክዳን ማሸጊያ ቁልፍ ሳይነካ የጎን ማሸጊያዎቹን በጥንቃቄ በመቀስ ሰብሮ ይከፍታል፤

ሐ) ድምፅ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች በሙሉ ከድምፅ መስጫ ሳጥን ቆጠራ ወደሚደረግበት ጠረጴዛ በመገልበጥ የምርጫ አስፈጻሚዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ ፊታቸው ወደታች እንደተዘቀዘቀ ለየብቻ ሀምሳ ሀምሳ እየቆጠረ እንዲመድቡ ያደርጋል፤

መ) ጊዜያዊ ድምጽ የተሰጠባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በአንድ ኤንቨሎፕ ውስጥ ተደርገው ለብቻቸው እንዲመደቡ ያደርጋል፤

ሠ) በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ የተገኙ የአንድ ምክር ቤት ምርጫ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች አጠቃላይ ብዛት በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘግባል፤

ረ) ጊዜያዊ ድምፅ የተሰጠባቸው ኤንቬሎፖች/ፖስታዎች አጠቃላይ ብዛት በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጹ ላይ ይመዘግባል፤

ሰ) በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ የተገኙ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች እና ጊዜያዊ ድምጽ ታሽጎ የተቀመጠባቸው ኤንቨሎፖች ድምር በመራጮች መዝገብ ላይ ከሚታየው ድምጽ የሰጡ መራጮች ብዛት ጋር አንድ አይነት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ከሳጥን ውቺ ወድቀው የተገኙ ድምፅ መስጫ ወረቀቶች ሲኖሩ ማመሳከሩ ከመፈፀሙ በፊት የነዚህ ወረቀቶች ቁጥርበመኣቾች መዝገብ ላይ ከተገኘው የመራጮች ብዛት ላይ መቀነስ ይኖርበታል፡፡ በሁለቱ ድምሮች መካከል አለመጣጣም ከተከሰተ በቦርዱ በተቀመጠው የቆጠራ ስርዓት መሰረት ተመሳክሮ ውጤቱ በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

2. ከላይ የተገለጹት ሂደቶች ለአንዱ ምክር ቤት ምርጫ ከተከናወኑ በኋላ የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ በሃምሳ በሃምሳ ታሰረው ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ከገቡ በኋላ ሳጥኑ ታሽጎ የማሸጊያው ቁጥር ለዚሁ በተዘጋጀው ፎርም ላይ ይሞላል፡፡
3. ለሌላኛውም ምክር ቤት ምርጫም እንዲሁም ህዝበ ውሳኔ የተደረገ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) (2) ስር የተመለከቱት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡
4. የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ማመሳከር በሚከናወንበት ጊዜ የአንዱ ምክር ቤት ድምጽ መስጫ ወረቀት የሌላኛው ምክር ቤት ምርጫ ሳጥን ወይም ህዝበ ውሳኔ ድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ ከተገኘ ይህ የድምጽ መስጫ ወረቀት ከዚህ ሳጥን ወጥቶ በትክክለኛው ቦታ እንዲደመር ተደርጎ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጹም በዚሁ አኳኋን እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 43. <u>ያልተበላሹ እና ዋጋ አልባ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ስለመለየት</u>

1. የምርጫ ጣቢያው ድምፅ የተሰጠባቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በመዘርጋት በመቁጠሪያ ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጣል፡፡
2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለእያንዳንዱ የምርጫ አስፈጻሚ በአንድ ጊዜ ሀምሳ የሚደርሱ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን በመስጠት ምልክት የተደረገባቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ድምፁን ከፍ አድርጎ በማንበብ እና በማንሳት ድምጹ የተሰጠው እጩ ስም ካለበት ካርድ ስር እዲያስቀምጡ ያደርጋል፡፡

3. ዋጋ አልባ የሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተለይተው በአንቀጽ 47 በተመለከተው አሰራር መሰረት በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በድጋሚ እንዲታዩ ለብቻቸው ይመደባሉ፡፡

**አንቀፅ 44.** **<u>ስለዋጋ አልባ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች</u>**

ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ዋጋ አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡

ሀ) የመራጩ ማንነት በስም የተገለፀበት ከሆነ፣

ለ) የጣቢያው ድምጽ መስጫ ወረቀት ትክክለኛነት ማረጋገጫ ማሕተም ከሌለው፣

ሐ) ለምክር ቤቱ ሊመረጥ ከሚቻለው ተመራጮች ቁጥር በላይ ላላቸው እጩዎች ምልክት የተደረገበት ከሆነ፣

መ) ምንም ምልክት ያልተደረገበት ከሆነ፣

ሠ) መራጩ ማንን እንደመረጠ መለየት የሚያስቸግር ከሆነ፣

ረ) ህጋዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት ያልሆነ ማለትም በምርጫ ጣቢያው ያልተሰራጨ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ፣

ሰ) ከሳጥን ውጪ ወድቆ የተገኘ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ፡፡

**አንቀፅ 45.** **<u>የድምፅ ቆጠራ ሂደት</u>**

1. የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ በእጩ ተወዳዳሪዎች ተለይተው ከተመደቡ በኋላ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ዋጋ አልባ የተባሉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በትክክል ዋጋ አልባ ስለመሆናቸው እንደገና መርምሮ በማረጋገጥ እያንዳንዱን ዋጋ አልባ የሆነ የድምጽ መስጫ ወረቀት በጣቢያው ላሉ ሰዎች በማሳየት ዋጋ አልባ የሆነበትን ምክንያት ጮክ ብሎ ይናገራል፡፡
2. በሁለተኛ ጊዜ ቆጠራው ትክክለኛ ሆነው የተገኙት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ድምጹ የተሰጠው እጩ ስም ካለበት ቦታ ላይ እዲቀመጡ ይደረጋል፡፡
3. ዋጋ አልባ የሆኑት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በጀርባቸው ላይ ***"ዋጋ አልባ"*** የሚል ጽሁፍ ከተጻፈባቸው በኋላ እንደገና ከተቆጠሩ በኋላ ብዛታቸው በምክር ቤቱ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘገባል።
4. ዋጋ አልባ የሆኑት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረው ከተመዘገቡ በኋላ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ፥ የምርጫ አስፈጻሚዎች ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጡትን ትክክለኛ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ተራ በተራ እንዲቆጥሩ መመሪያ ይሰጣል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) ስር የተመለከተው ቆጠራ ሁለት ጊዜ በተለያዩ የምርጫ አስፈጻሚዎች ከተቆጠረ በኋላ የተገኘው ውጤት በምክር ቤቱ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይመዘገባል፡፡

6. ከላይ የተገለጸው የቆጠራ ሂደት ለእያንዳንዱ በድምጽ መስጫው ወረቀት ላይ ላለ እጩ ተወዳዳሪ በተመሳሳይ ሁኔታ ይከናወናል፡፡
7. እጩዎች ምንም ድምጽ ካላገኙ በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ዜሮ ይመዘገባል፡፡
8. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቦታው የተገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና የእጩ ወኪሎች ለምርጫው በተዘጋጀው የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡
9. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የአንዱ ምክር ቤት የድምፅ ቆጠራ ሲጠናቀቅ ቆጠራው መጠናቀቁንና የሚቀጥለው ቆጠራ የሚጀመር መሆኑን ህዝበ ውሳኔ የተደረገ ከሆነም ከምክር ቤቶቹ ቆጠራ በኋላ የሚከናወን መሆኑን ለሁሉም ማሳወቅ አለበት፡፡
10. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 8 ስር የተደነገገው ቢኖርም በድምፅ አሰጣጡ፣ በቆጠራው ወይም በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው የእጩ ወኪል ቅሬታውን በምርጫ ጣቢያው አስመዝግቦ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይፈርማል፡፡

## አንቀፅ 46. <u>የክልል ምክር ቤት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ቆጠራ ሂደት</u>

1. የዚህ መመሪያ አንቅ 45 እና 47 ድንጋጌዎች ቢኖሩም በክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ከአንድ የምርጫ ክልል ከአንድ በላይ እጩዎች የሚመረጡ ስለሆነ የክልል ምክር ቤቶች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቆጠራ ሂደት የሚከተሉት ተጨማሪ ሂደቶች ይከናወናል፤

   ሀ) በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ወረቀት ለእያንዳንዱ እጩ ተወዳዳሪ የተሰጠው ድምጽ ጮክ ብሎ ከተገለጸ በኋላ የተሰጠው ድምጽ በተጠቀሰው የእጩ የውጤት መቁጠሪያ (መመዝገቢያ) ቅጽ ላይ ይመዘገባል፡፡

   ለ) ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠው ድምጽ በየውጤት መቁጠሪያ (መመዝገቢያ) ቅጽ ላይ ይደመራል፡፡

   ሐ) በሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ የተሰጠው ድምጽ ከተመዘገበ በኋላ እያንዳንዱ እጩ ተወዳዳሪ ያገኘው ውጤት በምክር ቤቱ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ይሞላል፡፡

## አንቀፅ 47. <u>የውጤት ማመሳከሪያውን በግልጽ ስለማሳየትና ስለማሸግ</u>

1. የእያንዳንዱ የምርጫ ዓይነት (ምክር ቤት) የድምፅ መስጫ ወረቀት ለየብቻ ከተቆጠረና በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጽ ላይ ከተሞላ በኋላ አንድ ቅጂ ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ቦታ ይለጠፋል፤ ዋናው ቅጂ ቢከፈት መከፈቱ በሚያስታውቅ ማሸጊያ ውስጥ ታሽጎ ለድምጽ ማዳመሩ እንዲያገለግል በምርጫ ጣቢያው ሀላፊ አማካይነት ለምርጫ ክልሉ በተገቢው የርክክብ ሰነድ መሰረት እንዲረከብ ይደረጋል፤ አንድ ሌላ ቅጂ መከፈቱ በሚያስታውቅ ቦርሳ ውስጥ ተከተው ከድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ ጋር በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ይቀመጣል፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጾቹን ግልባጭ በመሙላት በጣቢያው ለተገኙ ታዛቢዎችና ፣ የዕጩ ወኪሎች ይሰጣል፡፡

### አንቀፅ 48. <u>የድምፅ ቆጠራ የማይቋረጥ ስለመሆኑ</u>

በምርጫ ጣቢያ የማንኛውም ምርጫ የድምፅ ቆጠራ በምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሣኔ ካልሆነ በስተቀር ሊቆም ወይም ሊቋረጥ አይችልም።

### አንቀፅ 49. <u>የድምፅ ቆጠራ ውጤትና የምርጫ ቁሳቁስ መልሶ ስለመላክ</u>

የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በጣቢያው ማንኛውም አይነት ምርጫ የተከናወነባቸው የሚከተሉትን ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን በቦርዱ የምርጫ ማስፈጸሚያ ቁሳቁሶችና እና ሰነዶች ድልድል፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብና አወጋገድ መመሪያ መሰረት በማሸግ በጸጥታ አካላት እጀባ ለምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ያስረክባል፡

1. በሳጥን ውስጥ ተገኝተው የተቆጠሩ ድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለየብቻ ተለይተው፣
2. በጥቅም ላይ ያልዋሉ፣ ዋጋ አልባ የሆኑ እና ከሳጥን ድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣
3. የመራጮች መዝገቦች፣
4. የድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያና ውጤት ቅጾቹ ከተከፈተ መከፈቱ በሚያስታውቀው ማሸጊያ ታሽገው በሳጥኑ ጎን ላይ በፕላስተር እንደተጣበቁ፣
5. ያልተቆጠሩ ጊዜያዊ ድምፅ የተሰጠባቸውን ፖስታዎች እንደታሸጉ፣
6. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራው እንደተጠናቀቀ የየምርጫውን ዓይነት የቆጠራ ውጤት ማሳወቂያ ቅፅ እና የመክፈቻ እና መዝጊያ ቃለጉባዔዎች በፖስታ እንደታሸጉ፣
7. ልዩ ልዩ የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## <u>የምርጫ ክልል ድምፅ ማዳመር እና ውጤት አገላለፅ</u>

### አንቀፅ 50. <u>የድምፅ ቆጠራ ውጤት ማዳመር</u>

1. በምርጫ ክልል የሚገለፅ የድምፅ ማዳመር የየምርጫ ጣቢያው የድምፅ ቆጠራ ውጤት ተጠናቆ እንደደረሰ እጩዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት ውጤቱን በቦርዱ የተቀመጠውን የቆጠራ ስርዓት በመከተልና በማዳመር ለዚሁ በተዘጋጀው ቅፅ በመሙላት ይሆናል፡፡ የምርጫ ክልሉ የምርጫ

አስፈጻሚዎች በምርጫ ክልሉ የተገኘውን ውጤት ከምርጫ ጣቢያ ውጤት ዝርዝር ጋር እንደደረሳቸው ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ካላጋጠመ በስተቀር ቆጠራው በተጠናቀቀ በ5 ቀናት በምርጫ ክልሉ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ለህዝብ እንዲገለፅ ያደርጋሉ፡፡

2. እንደአግባብነቱ ቦርዱ በሚያወጣው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም መመሪያ መሠረት በምርጫ ክልል በወረቀት ላይ ከሚካሄደው ማዳመር ጎን ለጎን ኤሌክትሮኒካዊ ማዳመር ሊከናወን ይችላል ፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ለምርጫ ክልሉ የድምፅ ቆጠራ ውጤት ከዝርዝር ሪፖርት ጋር ከምርጫ ጣቢያው እንደደረሰ ለድምፅ ማዳመር ሂደቱ ከምርጫ ጣቢያ ወደ ምርጫ ክልል በቀረበው ሪፖርት ላይ ተገቢው ምርመራ መደረግ አለበት።
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 3 መሰረት ምርመራ ሲደረግ ከየምርጫ ጣቢያው ወደ ምርጫ ክልል በተላከው የድምፅ ማመሳከሪያና ውጤት ቅፅ እና በድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ በተገኙ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች መካከል ልዩነት ከተገኘና በድምፅ መስጫ ሳጥን ውስጥ የተገኙት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች እና በመራጮች መዝገብ ላይ ያለው የተጣራ የፊርማ ብዛት መካከል ያለው ልዩነት በቁጥር ከ10 ያልበለጠ ከሆነ የማዳመሩ ስራ እንዲቀጥል ይደረጋል።
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት በተደረገው ምርመራ መሰረት የልዩነት መጠኑ በቁጥር ከ10 የበለጠ ከሆነ ከምርጫ ጣቢያ የተላከው የድምፅ ማመሳከሪያና ውጤት ቅፅ ተለይቶ እንዲቀመጥ ተደርጎ ተጨማሪ ምርመራ መደረግ አለበት። ተለይቶ በተቀመጠው የድምፅ ማመሳከሪያና ውጤት ቅፅ ላይ ድጋሚ ምርመራ ተደርጎ የልዩነት መጠኑ ከ10 በላይ መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብ ባለው የህግ ማዕቀፍ መሰረት ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል።
6. በአዋጁ አንቀፅ 154 ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ስልጣን ካለው የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም በአዲስ አበባና በድሬዳዋ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሣኔ ለምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ካቀረበ የሰጠው ድምፅ እንዲዳመር ይደረጋል።
7. በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ በአዋጁ አንቀጽ 55 እና 154 ንኡስ አንቀጽ (3) እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 በተመለከተው መሰረት ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ስልጣን ላለው ለወረዳ ፍርድ ቤት ወይም በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱም የድምጽ መዳመሩ ሂደት ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል።
8. የምርጫ ክልሉ ኃላፊ:

   ሀ) የምርጫ ክልሉን የምርጫ ድምር ውጤት መተማመኛ ለእጩዎች ወይም ለወኪሎቻቸው በማስፈረም መስጠት አለበት።

   ለ) የምርጫውን ድምር ውጤትና አጠቃላይ ሪፖርት ለቦርዱ ጽሕፈት ቤትና በየደረጃው ለሚገኙ የበላይ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መላክ አለበት።

## አንቀፅ 51. <u>አሸናፊውን ለመለየት ያልተቻለ እንደሆነ</u>

በምርጫ ክልል ውጤት ከተደመረና ቅሬታዎች እልባት ካገኙ በኋላ ዕጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ ከፍተኛ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ ይካሄዳል።

## አንቀፅ 52. <u>የተመራጭነት መታወቂያ ወረቀት ስለመስጠት</u>

በምርጫው አሸናፊ ለሆነው ዕጩ እንደምርጫው አይነት የተመራጭነት መታወቂያ ካርድ በምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ተሞልቶ ይሰጠዋል።

## አንቀፅ 53. <u>በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚቀርብ ተቃውሞ</u>

1. በድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ፣ ማዳመር እና ውጤት አገላለፅ ሂደት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በአዋጅ ቁጥር 1162 ክፍል ሰባት ላይ በተዘረዘረው እንዲሁም ቦርዱ ባወጣው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 10/2013 መሰረት ውሣኔ ያገኛሉ።
2. በምርጫ ጣቢያው ወይም በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የድምጽ ቆጠራው ሁኔታዎች እስኪጣሩ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ሊደረግ ይችላል። ማንኛውም ድጋሚ ቆጠራ መከናወን ያለበት በዚህ መመሪያ በተደነገገው የቆጠራ ስርዓት መሆን አለበት።
3. በቆጠራው ሂደት ላይ ተቃውሞ ከቀረበ በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 155 ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ውጤቱ እንዳይገለጽ ይደረጋል።
4. የምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያ ሀላፊዎች ለጽሕፈት ቤታቸው የቀረቡ ቅሬታዎችና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ ውሣኔዎችን ዋና ቅጂ እና የፅሑፍ ማስረጃዎችን ፋይል አድርገው መያዝ አለባቸው።

## አንቀፅ 54. <u>በቦርዱ ስለሚገለፅ ጊዜያዊ የምርጫ ውጤት</u>

1. ቦርዱ የጠቅላላ ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠቃሎ እስከሚደርሰው ድረስ ከየምርጫ ክልሉ የሚመጣለትን የምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ይፋ ሊያደርግ ይችላል። ውጤት ይፋ የማድረግ አስፈላጊነት በቦርዱ ከታመነበት ይፋ የተደረገው ውጤት የውሱን የምርጫ ክልሎች ውጤት መሆኑ በግልፅ መመልከት ይኖርበታል።
2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የምርጫ ክልሎችን የምርጫ ውጤት የሚገልጸው የመጨረሻ የምርጫ ውጤት በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለመግለጽ የማይችል ከሆነ ነው።

## **አንቀፅ 55.** **<u>ስለአካባቢ ምርጫ ውጤት አገላለፅ</u>**

1. ከላይ በአንቀፅ 56 ስለምርጫ ውጤት አገላለፅ የተደነገገው እንዳግባብነቱ ለአካባቢ ምርጫ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ቦርዱ የአካባቢ ምርጫ ውጤት በክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በጊዜያዊነት እንዲገለፅ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የአካባቢ ምርጫ ውጤት በክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሲጠቃለል አጠቃላይ የውጤቱ ሪፖርት ለቦርዱ መላክ ይኖርበታል፡፡

## **አንቀፅ 56.** **<u>በቦርዱ ስለሚሰጥ ይፋዊ መግለጫ</u>**

1. የጠቅላላ ምርጫ ሂደት ተጠናቆ ቦርዱ የተጠቃለሉ የምርጫ ውጤቶች እና አስፈላጊ መረጃዎች ከሁሉም የምርጫ ክልሎች ከተሰባሰቡ በኋላ ቦርዱ የመጨረሻውን የምርጫ ውጤት ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ካላጋጠመ በስተቀር ምርጫው በተጠናቀቀ በ10 ቀናት ውስጥ ለህዝብ በይፋ ይገልጻል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ክልል ደረጃ በተገለጹ ውጤቶች ላይ የቀረቡ አቤቱታዎች ውጤት መግለጹን እንዲዘገይ የሚያደርግ ከሆነ ይፋዊ ውጤት የሚገለጽበት ጊዜ እስከ 20 ቀን ድረስ ሊዘገይ ይችላል፡፡
3. ቦርዱ የሚሰጠው ይፋዊ የውጤት መግለጫ የሚከተሉት ነጥቦች ያካተተ ይሆናል፡፡
    - ሀ) በምርጫው የተመዘገቡ መራጮች ብዛት፣
    - ለ) በምርጫው ድምፅ የሰጡ መራጮች ብዛት፣
    - ሐ) በምርጫው ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ ተመዝጋቢ መራጮች በመቶኛ፣
    - መ) ለየምክር ቤቱ የተመረጡ ዕጩዎች የስም ዝርዝር፣
    - ሠ) የተመረጡ ዕጩዎች የተመረጡበት የምርጫ ክልል፣
    - ረ) የፖለቲካ ድርጅቶች ለየምክር ቤቱ ያገኙት መቀመጫ ብዛት፣
    - ሰ) ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉና የተበላሹ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣
    - ሸ) እያንዳንዱ ዕጩ በየምርጫ ጣቢያ ያገኘው የድምፅ ውጤት እና ሌሎች መረጃዎች ከምርጫ ክልሉ እንደደረሰውና አጠናቅሮ እንደጨረሰ ይፋ ያደርጋል፡፡
4. ቦርዱ የአካባቢ ምርጫ ሂደት ተጠናቆ እንደደረሰው እንደአግባብነቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) ስር በተዘረዘረው መሠረት ይፋ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ አስር

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀፅ 57. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ የዚህን መመሪያ አፈፃፀም በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**አንቀፅ 58. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከግንቦት 3 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ